# ወያኔነት ሃገር የማፍረስ ተግባር እንጂ.......

ታዛቢው ከሆላንድ

የዚህ ጽህፍ ዓላማ ወያኔነት ፣ በአሁኑ ወቅት፥ ሃገር የማፍረስ ፥ ወይም ኢትዮጵያዊንትን የማዳከም ትግባራዊ እንቅስቃሴ እንጂ ብዙዎች በተለምዶ እንደሚያስቡት ፥ ወያኔነት ትግሬነት ወይም ከአንድ ጎሳ ጋር ብቻ የተያያዘ አለመሆኑን ለማሳየት ነው ፡፡

ለመንደርደሪያ ባጭሩ ፥ ወያኔነት ምንጬ ፥ አመጣጡ ፥ አፈጣጠሩ ሁሉም እንደሚያውቀው ባጭሩ ፥ ከተወሰኑ ከትግራይ አካባቢ ፥ ንጉሱ ከስደት ከተመለሱ ቦኋላ ስልጣኑን አማራ ወይም ሸዋ ወሰደው በሚል ፥ ስልጣን ይገባናል ብለው ለአምጽ ተንቀሳቅሰው ቶሎ የተመቱበት ሁኔታ ሲኖር ፡፡ በኛ ዘመን ደግሞ ትግሬን ነፃ እናወጣለን ብለው የተነሱት እነ አቶ መለስ ፥ ወያኔ የሚለውን ስም ይዘው ሲቀጥሉ ፣ እንደ በፊቶቹ በአንድ ዘር ላይ ያነጣጠረ የጥላቻ ፖለቲካ ማካሄዳቸውና ፥ የስልጣን ይገባናል ጥያቄው እንደ በፊቱ ይሁን እንጂ ፥ የአሁኖቹን የትግሬ ነጻ አውጪዎች ከአባቶቻቸው ልዩ የሚያደርጋቸው ፥ ሃገር ለመገንጠልና ለማስገንጠል ባጠቃላይ በጸረ ኢትዮጵያዊነት አቅዋም በገሃድ በመቆማቸው ነው ፡፡

ትግራይን ከደርግ ``ነፃ`` አውጥተው የትም መድረስ እንደማይችሉ ቶሎ ገባቸው፡፡ የሃገሪቱን ስፋት ከሕዝቡ ብዛት እነሱ ብቻቸውን ለመሸፈን እንደማይችሉ ፣ ቢሮክራሲውን በስፋት ለመቆጣጠር የሚያስችል የተማረም ሃይልም ሆነ ፥ ሃገሪቱን ከዳር እስከዳር ለመቆጣጠር የሚያስችል ወታደር አልነበራቸውም ፡፡ በዚህም ምክንያት ዘዴያቸውን ቀይረው ፥ ኢትዮጵያን ባዲስ መልክ ማለትም በቋንቋና በጎሳ ላይ የተመሰረተ ፌዴሬሽን ከምርኮኞችና ፥ ከተገንጣይ የጎሳ መሪዎች ተወካይ አውጣጥተው የውሸት ኢትዮጵያዊነት ካባ አጥልቀው ፥ አዲስ ስርአት መሰረትን ብለው ማተራመሱን ጀመሩ ማለት ነው ፡፡

ወያኔነት መሰረቱ ጸረ ኢትዮጵያዊነት ነው ስንል ፥ ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለውን መንገድ መሆኑን ካየ ፥ በሕዝባችንና ፥ በመሬትዋ ፥ በእምነታች፥ በታሪካችን ላይ ችግር ለመፍጠር ማንኛውንም የጭካኔ መንገድ የሚወስድ ማለት ነው፡፡ እነ አቶ መለስ ፥ የሃገር ፍቅር ፣ ብሔራዊ ስሜት ፥ መርህ ፥ ከሚባሉት ተግባርም ሆነ ቃላት ጋር ሆድና ጀርባ ናቸው ፡፡ እነ አቶ መለስ ፥ ወያኔ ይዞ ተነስቶ የነበረውን ``ዓላማ``ና አብረውት የተዋደቁለት ጉዋዶቻቸውን ፥ እስከ የስልጣን አጋሮቻቸው እንደ ያደፈ ፎጣ በየሳምንቱ እየቀያየረ ከደደቢት ተነስቶ ሞሳ እየሰራ እያታለለ እራሱ ኳስ ሆኖ

ወደ ኬንያ እስከሚገባ ድረስ ለጊዜው ደቡብ ደርሷል ፡፡ ስለዚህ የዚህ ትንሽ ጽሁፍ አላማና ፥ ማሳሰቢያ ባሁኑ ወቅት ወያኔነት ፣ ኢትዮጵያዊነትን ማዳከሚያ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ነው ካልን ፥ ይህን ተግባራዊ እንቅስቃሴ በያለንበት አካባቢ ነቅተን ለመከታተልና ተባብረንም ለማምከን እንድንችል ፥ ከምንኖርበት አካባቢና ከሌሎች ያየናቸውንና የታዘብናቸውን ለወገኖቻን ለማካፈልና ፥ አጥፊዎቹም በሃገር ቀልድ እደሌለና ለሚሰሩት አፍራሽ ተልኮ እያንዳንዳቸው በሃላፊነት እንደሚጠየቁበት መልዕክትም ጭምር ለማስተላለፍም ነው ፡፡

በመጀመሪያ ወያኔ በስልጣን ላይ መቆየት የሚጠቀምበት አንዱ ዘዴው በሀገራችን ውስጥም ሆነ እዚህ ውጪ በምንኖርበት የስደት ሃገር የማያቋርጥ ቀውስ ፤ ትርምስና ፤ መከፋፈል ፣ በሕዝባችን መሃከል መፍጠር ነው ፡፡
የነዚህ ነገሮች አለመኖር ለወያኔ ህልውና አስጊ ነው ፡፡ አብዛኛው ሕዝባችን ስለሚቃወማቸው ወያኔ ስልጣኑን የተቆጣተረው በሃይል ነው ፡፡
መሰረቱ አናሳ ስለሆነ ፥ ዲሞክራሲ ፥ ምርጫ ፥ ህብረት ፥ ብዙሃን ፥ እርቅ ፥ ሰላም ፣ የመሳሰሉት ለመጥፊያቸው ምክንያቶች ስለሆኑ ማንኛወንም ከፍተኛ ዋጋ ከፍለው በጀሌዎቻቸው አማካኝነት ስራ ላይ እንዳይውል እንደሚጥሩና ፥ እያደረጉትም እንደሆነ በሃገር ውስጥም ሆነ በየአካባቢያችን እየታዘብን ነው ፡፡

ወያኔ ስልጣን የያዘ አካባቢ ይህን ትርምስና ህዝባችንን መከፋፈል እስከተወሰነ ደረጃ በትግሬ ወያኔዎች ተጠቅመዋል ፡፡ ሆኖም ኤኮኖሚውን ሙሉ በሙሉ ከተቆጣጠሩ ቦኋላ የትግሬ ወያኔዎች ስራ ፥ በማንኛውም የመንግስት ፥ በሲቪሉም ሆነ በወታደራዊው ዘርፍ ቁልፍ የስልጣን እርከን ጨብጠዋል ፡፡ በከፍተኛ የንግድ ተቋሞች ወስጥ ከሕዝባችን ከሚዘረፈው ገንዘብ በነቂስ በሚመረጡ የአንድ አካባቢ ጎሳዎች፥ በመላው ዓለም በኢንቨስትመንት ስም በየአህጉራቱ በሚያስቀምጧቸው የገንዘብ ዘርዛሪ ወኪሎቻቸው አማካይነት፣ ከውስጥ የሚዘረፈውን በምንዛሪ ስም እያወጡ ንግዳቸውን አስፋፍተዋል ፡፡ በየዘመዶቻቸው ስም ከሃገራችን በሚዘርፉት ሃብት ንብረት በመግዛት ለልጅ ልጆቻቸው የሚበቃ ሃብት አከማችተዋል ፡፡ ወደፊትም ከነልጅ ልጆቻችን ሊገዙን ስለወሰኑ ፣ ሃብታችንን ብቻ ሳይሆን የሚዘርፉን ፣ በየጊዜው የሚገኘውንም የትምህርት ዕድል ሚዛኑን ባልጠበቀ መንገድ ፥ከነሱ የዘር ግንድ ብቻ ለሚወጡ በገፍ ዕድሉን ሲሰጡ አይተናል ፡፡

ሃገር ውስጥ ፊርማ ለመፈረምና እንግዳ ለመቀበል ብቻ የውጭውን አለምና ሕዝባችንን ለማታለል ለሽፋን የሚሾሙት (እራሳቸው ተሿሚዎቹም ያውቁታል) ከፊት እንደ ፕሬዘዳንት ፥ ዋና ሚኒስቴር ፣ ኮሚሽነር፥ ጄነራል .....ወዘተ እያለ ሊያጭበረብርባቸው ይሞክር እንጂ ፥ ዋናው ስልጣን ያለውና ፣ ማንኛውንም ትእዛዝ ፣ የሚተላለፈው ፥ ታኮ የሚባሉት ከዋናው ስር በምክትልነት ያሉት የአንድ ብሄር ተወላጆች እንደሆኑ የነፈሰበት ሚስጥር ነው፡፡

እንግዲህ ሃገር ውስጥ ሕዝባችንን በሃይል አፍኖ እንደተቆጣጠረው በውጭው ዓለም ዙርያ በስደት በያለንበት ሃገር ሕዝባችን ላይ የሚያደርሰውን በደል ተባብረን ለዓለም መንግስታት እንዳናሳጣው ፣ ወይም በኛም መሃል ህብረት ፈጥረን በጋራ የተሻለ መፍትሄ ለሃገርችን እንዳንፈልግ ፥ ማንኛውንም ዋጋ ከፍለው ሊበታትኑን እንደወሰኑ የተለያዩ መረጃዎችን ብቻ ሳይሆን በተግባርም በያለንበት እያየን ነው ፡፡

ይህንን እቅዳቸውን የሚያስፈጽሙት በተጨባጭና በተደጋጋሚ እንዳየነው በግልጽ በምናውቃቸው ወኪሎቻቸው ሳይሆን ፥ እዚህም ውጭው ዓለም እንደኛው አገአዙ ችግር አደረሰብን ብለው በተሰደዱት፥ተቃዋሚ ነን በሚሉ አብረው ከኛ ጋር ከሚበሉ፥ከሚጠጡ በቅርብ ከምናውቃቸው ሰዎች ነው ፡፡ በረቀቀ መንገድ መመሪያ እየስጥዋቸው ከወያኔዎቹ የተራረፈ ትናንሽ ፕሮጀክቶች ፍርፋሪ የሚጣልላቸው አንዳንድ ለንዋይ ሞራላቸን ለለወጡ ውጪ በሚገኙ ፕሮጅርክቶችና ፥ የንግድ ተቋሞች ፥ የተወሰኑ የኢትዮጵያ ሬስቶራንት ባለቤቶች ሽፋን እየተጠቀሙ የወያኔን ንግድ ለፈረንጁ ያስተዋውቃሉ፡፡ በሃገሪቷ ሰላም ፥ ዴሞክራሲና የተረጋጋ ሁኔታ እንዳለ ፥ የፈረደበት ፎቅና ድልድይ ፥ መንገድ እየቆጠሩ ምስክርነታቸውን እያሰሙ ግልጋሎታቸውን በመስጠት ሕዝባችንን ያዘርፋሉ ፥አብረውም ይዘርፋሉ ፡፡

ትግሬ ወያኔዎቹ አገዛዙን እንደሚደግፉ ብዙ ጊዜ በቀላሉ ሰዎች ስለሚጠረጥሯቸው፣ እነሱም መደበቁን ስለማይችሉ ፥ ትግስቱም ስለሌላቸው ፥ በግልጽ የመከፋፈሉን ስራ ወያኔ ለነሱ መስጠቱን ትተዋል ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ የትግሬ ወያኔዎች፥ በከፍተኛ የስልጣን እርከብ፥ በንግድ፥ በስለላ ፥ አንዳንዴም ወያኔን በሚደግፉ ሰልፎች እንጂ፥ ወደ ህዝብ ወርዶ የመከፋፈሉን ስራ የሚያስፈጽሙት ትግሬ ባልሆኑ ከሌሎች ብሄረሰቦች ነው ፡፡

ብዙ ሆዳም ልክስክሶች በነቂስ ደካማ ብልታቸው እየተፈለገ ለገንዘብ ፥ ለስልጣን ያበዱና ፥ የአልኮል ፥ የአደንዛዥ ዕፅና ፥ የሴት ሱስ የተናውጣቸውን ግለሰቦች ለዚህ አይነት ወራዳ ተግባር የተመቻቹ ናቸው ፡፡ በተለይ አንዳንድ ባለፈ ታሪካቸውም ለመጣው አገዛዝ ሁሌ የሚያጎበድዱ ፥ ታሪካቸው እየተጠና፥ በባትሪ እየተፈለጉ ሆዳቸውን እየሞሉላቸው የመከፋፈሉና የማራኮቱን ስራ ያስጀምሩዋቸዋል ፡፡ ተረቱ (ድመት መንኩሳ አይጥ ሙብላትዋን ላትረሳ) እንደሚባለው ፥ ለሆዳቸው ሲሉ ከየመጣው መንግስት ጉያ ሊወሸቁ ሲሞክሩ በተደጋጋሚ የታዘብናቸው ብዙ ናቸው ፡፡

ሌሎቹ አንዳንድ ወደ ሃገርግ ቤት በኢንቨስትሜንት ስም ገባ ወጣ እያሉ ለሚሰሩት ቁሳቁስ እንደ ቤት ፣ ትራንስፖርት ፥ ንግድ ፥ ወፍጮ የመሳሰሉትን ወያኔ እንዳትወርስባቸው ስለሚፈሩ በወዶ አደርነት ከቻሉ በድብቅ ካልቻሉ በግልጽ ሎሌነታቸውን ይጀምራሉ፡፡ ወያኔም ድክመታቸውን ስለምታውቅ ፣መሬት ተመርተው ገና ነዋያቸውን ማፍሰስ ሲጀምሩ ቀርበው እከክልኝ እንዳከልህ ግዴታ ወስጥ ያስገቡዋቸዋል፡፡ ሆኖም አብዛኛው ወገናችን በቆራጥነት ይህን ደባ ባለመተባበር ፈተናውን ሲያልፍ ፣ጥቂት

የማይባሉ የናት ሆድ ነካሾች ፣ ለጥቅም ጀርባቸውን አጉብጠው የህዝባችንን መከራ ለማራዘም ላገዛዙ ማደር ይጀምራሉ ። ብዙ ጊዜ ወያኔዎች አንዴ ሞራሉን ለሸጠ ወራዳ ይሉኝታ ስለሌላቸውና ፥ እንደሚፈሩ ስለሚረዱ በተደጋጋሚ እንደታየው በግልጽ ወጥተው በየአደባባዩ ለወያኔ ለድጋፍ ሰልፍ እስከ ማስጮህ አድርሰዋቸዋል ። በየሱቃቸው፣ በየመደብራቸው የወያኔን የንግድ ማስታወቂያዎች ያሰሯቸዋል ። በየወያኔው ድግስ ምግብ እንጀራ እንዲሸጡና ፥ የነጻ ምግብና አልኮል ሆዳቸውን እየሞሉላቸው ተቆጣጥረዋቸዋል ።

እንዲያውም የወያኔ የንቀቱ ንቀት ፥ በየትኛውም ዓለም ተሰምቶ የማይታወቅ ፥ ማንኛውም ከሃገር ውጪ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ፥ ሃገር ውስጥ ፥ ቤት ወይም ሌላ ንብረት ያለው ፥ ሃገር ወስጥ ገብቶ ማንነቱን ፥ ለታክስ አከፋፈልና ፥ አሸባሪ አለመሆኑን ለማረጋገጥ በሚል ፥ ተጠርቶ ገብቶ አሻራ እንዲሰጥ ብለው አዲስ መመሪያ ሲያወጡ ፣ እነዚህ በጥቅም የያዝዋቸውን ለንብረታቸው ብለው ፈርተው ምንም አይነት ወያኔን የሚቃወም እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፉና ማንኛውንም ተእዛዝ እንደሚቀበሉ በማመን ነው ።

ከዚህ በላይ ወይም ታች ዝቅ ብሎ የሚያመላክተው፥ በቀጥታ በፈቃደኛነት ወያኔን የሚተባበሩትን እንጂ ፥ ሀገሩ ናፍቆት ወገኑን ለማየት ወይም ለመርዳት ሃገር ወስጥ የሚገባውን ወይም ፥ ከወያኔ መዋቅር ውጪ ለሕዝባችን የሚጠቅም ስራ የሚሰሩትን በጅምላ ስህተት ነው ፥ ወይም ወያኔን ይደግፋል ማለታችን እንዳልሆነ ግልጽ ማድረግ እንፈልጋለን ።

እነዚህ ወራዳ ሆድ አደሮች ለግል ጥቅማቸው ብለው ሕዝባቸውን እንደ ከዱ ውስጣቸው ስለሚረብሻቸው፥ ነገ ሲታወቅባቸው ሊያጋልጡዋቸው ይችላሉ ብለው የሚገምትዋቸውን ሃገር ወዳድ ሰላማዊ ዜጎቻችንን ፥ ሊያስተበብሩ ይችላሉ ብለው የሚፈሩዋቸውን ግለሰቦች ፥ ወይም ይህን የባንድነት ተግባር የነቁባቸውን ፥ በሚያገኙት አጋጣሚ ሁሉ ስማቸውን ማጥፋት ፥ ሰዎች እንዲርቁዋቸው ማሳደምና ፥ ከዚያም በላይ አልፈው ብዙ ነገር ይሞክራሉ ።

ይህንንም ተግባራቸውን በተቻለ አጋጣሚ ሁሉ ወደ ወያኔ ጆሮ እንዲደርስ የተለያየ ዘዴ ይጠቀማሉ ወይንም በግልጽ ከሚታወቁ የወያኔ አባላት ጋር ፥ በሞደሬት ስም በየኮሚቴው ጀርባ ለጀርባ እየተሻሹ አብረው መስራት ይጀምራሉ። ``አናክርር ፣ ግማሽ መንገድ ሄደን እንቀበላቸው ፥ አንሸሻቸው`` ወያኔን የሚተካ ምን የተደራጀ አለ ? ተቃዋሚው አይተባበርም፥ ምናምን እያሉ አድርባይነታቸውን ለመሸፋፈን ይሞክራሉ ። ትናንሽ ድክመታችንን በማጋነን ካሁን በሃላ ተቃዋሚው ዋጋ እንደሌለው በማጣጣል ደካሞችን ከትግሉ ለማግለል ተስፋ ለማስቆረጥ ይሞክራሉ ። በነሱ ይባስ ብሎ የሚጠልዋቸውን ሰዎች በወያኔነት ለማስጠርጠር ይሞክራሉ፥ ከወያኔዎች ጋር ሞቅ ያለ ማህበራዊ ኑሮ እየኖሩ ፥ ማታ በየመሸታው ቤት አብረው ከበሮ እየደለቁ ፥ ቀን ለብተና

ተልኮዋቸው ጸረ ወያኔ ለመምሰል ይሞክራሉ ፡፡ አንዳንዶቹም ወያኔን ባደባባይ ስለሚቃወሙ ፥ አንዳንዴ ለሆዳቸው ማደር ሃጢያት አይደለም ብለው የሚገምቱ እንዳሉ ታዝበናል ፡፡ አገዛዙ አካባቢ ሃገር ውስጥ ያሉትን ወያኔዎች እንጂ `` ከኛ `` ጋር ተስማምተው ማህበራዊ ኑሮ የሚኖሩትን ``ጨዋ ወያኔዎች`` አትንኩዋቸው ያሉንም አልታጡም ፡፡ እነዚህ በጠራራ ፀሀይ ወያኔን እየተቃወሙ ፣ ምሽት ላይ ወያኔን `` አታለን ተጠቀምን `` በሚል ሽፋን እራሳቸውንና ሌሎችን ለማጃጃል የሚከጅሉትን አታሹፉ ግማሽ ልባችሁ ከጠላት ጋር ነው ልንላቸው ይገባል ፡፡ በጣም የሚገርሙት እነዚህ ባንድ ምሽት ሁለት አልጋ ላይ ተኝተው መንቃት የሚችሉትን ጉዶች ፥እንዴት ሁለት ተፃራሪ ነገሮችን በህሊናቸው አስማምተው አይናቸውን በጨው አጥበው ሲቀጥፉ ፥ ሲቀባጥሩ ሲያስመስሉ ሲዋሹ ስናይ ከሁለት አንዱን ምረጡ ልንላቸው ይገባል ፡፡

በብዙ የአሜሪካና የአውሮፓ ከተሞች በግልጽ እንደታየው ወያኔ የሚመለምሏቸው አዳዲስ ካድሬዎች አብዛኞቹ ከጥርጣሬ ለመዳንና የመከፋፈል ስራቸውን ሽፋን ለመስጠት በአንዱ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ያሉ ፥ የነበሩ ፥ ወይም ተልከው የተጠለሉ ናቸው ላለፉት አመታት በተለይ ወያኔ የመግደያ ወረዳ እይታ ውስጥ አስገብተው ይህንን መርዛቸውን በዘዴ እየረጩ ህብረታችንን የሚከፋፍሉት ፣ የዕምነት ቦታዎችን ፣ የመረዳጃ ማህበራትን ፥ የእስፖርት ተቋሞችን ፥ የሴቶችና የህፃናት ስብስቦችን ሁለት ቦታ እየከፈሉ ማናቆርና ፥ መበተን ነው፡፡

እነዚህ አስመሳይ ከፋፋዮች በስማችን ከሚዘርፉት ገንዘብና ፣ በሃይማኖት ፣ በባህላችን ከሚቀልዱት ባሻገር ፥ በፖለቲካውም ዘርፍ በውሸት የተጠለሉበትም የፖለቲካ ድርጀት ከሌላ ተቃዋሚ ድርጅት ጋር ግንባር ፈጥሮ የሃገሩን ችግር እንዳያግዝ ተቀራርበው በጋራ ወያኔ ላይ እንዳያተኩሩ ፣ ህብረት እንዳይፈጥሩ ከውስጥ ሆነው ፣ ጥቃቅን ልዩነቶችን በማናፈስ የውስጥና የግልጽ የወያኔ አርበኝነታቸውን ያከናውላሉ ፡፡ ይህንንም ዝም ተብለው የልብ ልብ የተሰማቸው አካባቢዎች ፣ ከዚህም አልፈው ሀገር አፍራሹን ወያኔን ድጋፍ ለመስጠት እስከ ሰልፍ የወጡባቸ አካባቢዎች እንዳሉ በግልጽ አይተናል ፡፡ ይህን ሁኔታ በየቦታው በቸልታ የምናየው ከሆነ ነገ በያለንበት ሃገር ተመሳሳይ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል አለማመን የዋህነት ነው ፡፡

ዕምነታችንን ማዳከምና ፣ ምዕመናንን መከፋፈል ኢትዮጵያን ማዳከም ነው ፡፡ በማንኛውም መንገድ ይህንን መደገፍ የወያኔን አጀንዳ ማራመድ ነው ካልን ፡፡ በሃገራችንና በዕምነታችን ሲቀልዱ ፤ ለሆዳቸው ሲገለገሉበት ስናይ ፥ ስንሰማ ፥ አይተን እንዳላየን ፥ ሰምተን እንዳልሰማን በለዘብተኝነት አይመለከተኝም ብለን እጃችንን አጣጥፈን መቀመጥ ፥ ሳናውቀው የነዚህ መሰሪዎች ተባባሪ መሆን ነው ፡፡ የኔን ፓርቲ ይደግፋሉ ፥ ወዳጄ ነው ፥ አበልጄ ነው ፥ እኔ ላይ በግል አልደረሱብኝም ፥ ለምን ልጠመድ ፥ የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ፥ በመሳሰሉት ደካማ ምክንያቶች እራሳችንን ብናታልል ወደድንም ጠላንም የምንጠቅመው ወያኔን ነው፡ የምንጎዳው የራሳችንን ወገን ነው ፡፡

ሕዝባችን እስከአፍንጫው ከታጠቀ አምባገነን ጋር ሃገር ውስጥ እየተዋደቀ፣ እኛ እዚህ ሰላም ፥ ዴሞክራሲ ፥ ህግ ያለበት ሃገር ውስጥ ቁጭ ብለን መብታችንን ማስጠበቅ አለመቻል በእውነቱ በራሳችን ልናፍር ይገባናል ፡፡ የሞቀ ቤታችን ቅጭ ብለን ስልኩ እስከሚቀልጥ ችግሩን ብቻ ብናወራ ፤ ኮምፒዩተር ፊት ለፊት ተቀምጠን ዓመቱን ሙሉ የፓልቶክ ማይክ እንደጡጦ ጨብጠን ወያኔን ብንራገም ፥ በየጉራንጉሩ ቡና ይዘን በጄ… ብንል ለራሳችን መደበሪያ እንጂ ለሕዝባችን መፍትሄ አይሆነንም፡፡ የተቃዋሚው ክፍል ወይም መራራቅ ለአገዛዙ ብቻ ስይሆን እዚህም ላሉት ወኪሎቻቸው መፋፋትና መጠናከር ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮላቸውል ፡፡

ከላይ እንደተጠቆመው ለነዚህ በታኝ አድር ባዮች የአረም ችግኛቸውን ለመዝራት የሚጠቀሙበት የአዝመራቸው ወቅት ፣ በፖለቲካ ድርጅቶች ፣ በመረዳጃ መህበራት ፣ በዕምነት ቦታዎች መጠነኛ አለመግባባቶች ሲፈጠሩ ፣ ስንጥቁን አስፍተው ፣ ወይ አስታራቂ መስለው ፣ ስራቸውን ሰደው ማናቆር ይጀምራሉ ፡፡ በዚህም የተነሳ ``ጭቅጭቅ`` የሚፈራው ፣ ነገር የሚጠላው ፣ አባላትና ፤ አማኞች ነገር በመፍራት ቤታቸው እንዲቀሩ ነው የሚፈለገው ፡፡ ይህንን ካመቻቹ ቦሃላ ፥ የማይጋፉዋቸውን ፥ ያልገባቸው የዋሆችን ፥ ወይም እነሱ ሊያሽከረክሩዋቸው እንችላለን ብለው የሚገምቱትን እያስመረጡ ሁኔታውን በቁጥጥራቸው ስር ያውሉታል ፡፡ ከዚህ ቦሃላ ማህበረሰቡን ያዳክሙታል ፥ አገዛዙን በማይቆረቁረው መንገድ ማመቻቸት ያያዙታል ፡፡

በሕዝባችን ላይ በሚደርሰው ኢሰባዊ ጉዳይ እንዳንነጋገር ፣ ስለሚገደሉ ፥ ስለሚታሰሩ ሰዎች እንዳይነሳ ፥ በጋራ ችግራችን ላይ እንዳናተኩር ፣``ይሄ ፖለቲካ ነው ሶሻል ማህበር ውስጥ አታንሱ `` `` ይህ ፕሮፓጋንዳ ነው ከስፖርት ጋር አይቀየጥ`` ``እነዚህ ፖለቲከኞች ናቸው እዚህ ውስጥ አይግቡ`` የመሳሰሉትን ትጥቅ አስፈቺ ማደናገሪያቸውን ይዘው ፥ አንዳንድ ሆዳሞችንም በትናንሽ ጥቅማ ጥቅም አፋቸውን በገንዘብ ሸብበው ሲቀልዱብን እስካሁን በትዝብት ብቻ እጃችንን አጣምረን በመቀመጣችን ፣ ማንኛችንም ከወቀሳ ልናምልጥ አንችልም ፡፡

ጎበዝ እነዚህ ደፋሮች በስማችን ሲዘርፉ ፣ በስማችን ሲነግዱ ፤ በስማችን እንግዶች ሲያዘርፉ ፣ በስማችን ለፖሊስ ፣ ለመንግስት መጥፎ ስም ሲያስጡን ፣ በስማችን ከወያኔ ጋር ንግድ ሲደራደሩ ፣ በያወያኔው ድግስ ንግዳቸውን ሲቸረችሩ ፥ አይተን እንዳላየ ፣ ሰምተን እንዳልሰማ እያስመሰልን፣ ``ማህበራዊ ኑሮዋችን እንዳይበላሽብን``ሰው እንዳየሸሽን ``ቡና አጣጪ እንዳናጣ `` የሃገር ቢቱ ፕሮጀክታችን እንዳይበላሽ እያልን ፥ እራሳችንን የምናታልል ካለን እኛም በተዘዋዋሪ ወያኔን እያጀብነው መሆኑን አንርሳ ፡፡

በእርግጥ ነገሮች ሳይገባቸው ፣ ወይም ለበጎ ተግባር መስሎዋቸው ሳያውቁ በየዋህነት የተሳሳቱትን ፣ ወገኖቻችንን ተንኮሉን አስረድተን መመለስ ይጠበቅብናል፡፡ ጭቅጭቅ ፣ ነገር ፈርተው በየቤቱ ዘግተው የተቀመጡትን ፣ ሽሽት ምፍትሄ ሊሆን እንደማይችል አሳምነን አውጥተን ከጎናችን ማሰለፍ ይገባናል ፡፡

ለማጠቃለል እንግዲህ ወያኔነት ሃገር የማፍረስ ተግባር እንጂ እንደድሮው ከአንድ ዘር ከትግራይ ጋር ብቻ የተያያዘ ፥ ወይም ከአንድ ቡድን የትግሬ ነፃ አውጭዎች ከነበሩት ወይም ከሆኑት ጋር ብቻ የተቆራኘ አይደለም ስንል ፥ የወያኔ አባል ሆንን አልሆንን በተግባር ወያኔ ስልጣን ላይ የሚያቆይብትን ከላይ የተዘረዘሩትን የማተራመስ ተግባር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አውቀንም ሆነ በስህተት የምንደግፍ ከሆነ ወያኔዎች መሆናችንን እንቀበል ፡፡ ሳናውቀው ከሆነ አንገታችንን እንደዚህ አይነት ዝቅጠት ውስጥ ያስገባነው ጊዜው ሳይመሽ እራሳችንን መርምረን እርምት እንውሰድ ፡፡

አገዛዙን ተቃውመን እዚህ በስደት ሃገር ለምንኖር ፣ የሃሳብ፣ የፖለቲካ፣ የዕምነት፣ ልዩነቶቻችን፣ ለሀገራችን አብረን እንዳንቆም እንቅፋት ሊሆን አይገባውም፡፡ አገዛዙና ፣ የአገዛዙ ጀሌዎች የጋራ ችግሮቻችን ናቸውና ፣ በጋራ ልናርማቸው ተገቢም አስፈላጊም ነው ፡፡ በተለይ አውቀው ለጥቅም እራሳቸውን የሸጡትን ፥ ማጋለጥና ከማንኛውም ማህበራዊ ግንኙነቶች ማግለል አለብን፡፡ እዚህ ብቻ ሳይሆን ሃገርም ውስጥ ማንነታቸውን ወዳጅ ዘመዶቻቸው የሚያውቁበት ዘዴ ከወዲሁ መፈለግ አለብን ፥ እነዚህ የጨነገፉ ግለሰቦች ሃገር ቤት ሲገቡ እራሳቸውን እንደተቃዋሚ ስለሚያቀርቡ ብዙ ወገኖቻችንን አሳስተው ላደጋ ሊያጋልጡዋቸው ይችላሉ ፡፡ ይህንን አይነት ቆራጥ አቅዋም ስንወስድ ነው የባንዳን መፈልፈያ ጉድጓድ የምንደፍነው ፡፡
ለኢትዮጵያ እንቆረቆራለን የምንል ይህንን አጠገባችን ያለውን ችግር ታግለን ማስወገድ ካልቻልን ምን ልንሰራ ነው ? ነገ ዛሬ ሳንል ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተን መፍትሄ ባስቸኳይ እንድንፈልግ ጥሪዬን አቀርባለሁኝ ፡፡

አባቶቻችን ድሮ የሚሉትን `` ጠላትማ ምንጊዜም ጠላት ነው አስቀድሞ....... አንርሳ

ኅብረታችንንአጠንክረን ከወገናችን ጎን እንቁም !!

ለከፋፋዮች እድል አንስጥ!! ዝምታ ያብቃ !!

Destabehager@gmail.com